# ጥቂት ነጥቦች ስለ ሽማግሌዎች ምርቃት

ሚያዝያ

ነሐሴ 10 ቀን 2001 ዓ.ም አንድነት ፓርቲ በአዳማ ከተማ የጠራውን ስብሰባ ለመረበሽ የወያኔ ወመኔዎች በጩከት ከተሰጧቸው ‹‹ምክንያቶች›› አንዱ ‹‹ስብሰባው በኦሮሞ ባህል መሠረት በሽማግሌዎች ምርቃት ስላልተከፈተ አንሰማም›› የሚል እንደነበር ተዘግቧል። የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ረብሻውን አምርረው ቢቃወሙም ስብሰባው በኦሮሞ ባህል መሠረት ቢከፈት ጥሩ ነበር ማለታቸው ደግሞ ተጨማሪ አግራሞትን ፈጥሮብኛል።

የሽማግሌዎች ምርቃት አድራጊ፣ ርግማናቸው ደግሞ አውዳሚ ነው የሚለው እምነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየከረረ መምጣቱ እና ከዚያም አልፎ በፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ መሣሪያነት እያገለገለ በመሆኑ በጉዳይ ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት መደረግ አለበት ብዬ ራሴን ካሳመንኩ ቆይቷል። ለአሁኑ ግን የአዳማው ክስተት ያጫሩብኝን አንዳንድ ነጥቦች በችኮላ ላንሳ።

ለመሆኑ የሽማሌዎች ምርቃት ሁሌ ጥሩ ነገር ነው? መጥፎ የሚሆንበት ጊዜ የለም? የፓርቲ ስብሰባዎች በሽማግሌ ምርቃት መከፈታቸው አግባብ ነውን?

ሁሉም ባህላዊ ልማድ ጠቃሚ ነው የሚል አስተዋይ ሰው የሚኖር አይመስለኝም። ችግሩ የሚጀምረው ጠቃሚና ጎጂ ልማዶችን ከመለየት ነው። ጠቃሚና ጎጂ ልማዶችን መለየት በበርካታ ምክንያቶች አስቸጋሪ ሥራ ነው። ከሁሉም በፊት በማን መመዘኛ ነው የሚፈረጁት የሚለው ጥያቄ መመለስ ከባድ ነው። አንዳንዱ ልማድ ደግሞ በአንዳንድ ሁኔታዎች ጥሩ፤ በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ መጥፎ ስለሚሆን ‹‹ጥሩ›› ወይም ‹‹መጥፎ›› ብሎ ወስኖ ማለፍ አይቻልም። ሌሎችም በርካታ ምክንያቶች መዘርዘር ቢቻልም ለጊዜው ይብቃን። ጠቃሚና ጎጂ ባህል ከተለየ በኋላ መምጣት ያለበት ጎጂ ልማዶችን ማስወገድ፤ ጠቃሚዎቹን ደግሞ ማዳበርና ማዘመን ነው። ጎጂ ልማዶችን ማስወገጃ የተለያዩ ስልቶች ቢኖሩም ለውጥ ፈላጊው ጎጂ ነው ያለውን ልማድ ባለመተግበር አርዓያ መሆን አንዱ የማይቀር ስልት ነው።

የሽማግሌዎች ምርቃት ‹‹ጠቃሚ›› ወይም ‹‹ጎጂ›› ብሎ መደምደም አስቸጋሪ ከሆኑት ባህላዊ ልማዶች አንዱ ነው ብዬ አምናለሁ። በበኩሌ ስለ ሽማግሌዎች ምርቃት ‹‹መለኮታዊ ሥልጣን›› የነበረኝ እምነት በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት አላለፈም። ሆኖም ግን አባቶችንና እናቶችን ማስደሰት የሚፈጥረው አዎንታዊ ድባብ እጅግ አስደሳች በመሆኑ ዛሬም የወላጆቼ ምርቃት እንዳይለየኝ እጥራለሁ።

በሌላ በኩል ግን ምርቃት ከአዎንታዊ ድባብና ስነልቦናዊ ሃሴት መፍጠሪያነት፤ ከምኞትና እርካታ መግለጫነት፤ ‹‹እሰይ አበጀህ፣ በርታ›› ከሚል ማበረታቻነት እና ከእርስ በርስ መሞጋገሻነት አልፎ የሌለውን ሚስጢራዊ ኃይል ሲላበስ ከዚያም አልፎ የአምባገነኖች የፕሮፖጋንዳ መሣሪያ ሲሆን ማየት በጣም እጅግ በጣም ያሳዝናል።

እኔ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ወደ ገጠር አዘውትሬ የምመላለስ ሰው ነበርኩ። በተለይ በማውቃቸው በምዕራብ ኦሮሚያና ጉራጌ ገጠሮች ገበሬዎች በአንድ ጠርሙስ አረቄ ምርቃት ‹‹ሥነ-ሥርዓት›› ገበሬዎች የሚያጠፉት ጊዜና ጉልበት እጅግ በጣም ያሳዝናል።

አንዳዶቹ ምርቃቶች ደግሞ ያስገርማሉ፤ ያሳፍራሉምም። ለምሳሌ ለሚከተሉት ‹‹ምርቃቶች›› ‹‹አሜን›› ትላላችሁ?

- የኢትዮጵያ ቁልፍ ኪስህ ውስጥ ይሁን!
- ጠላትህ ብን ብሎ ይጥፋ!

- በክፉ የሚያይህ ይህ ጨለማ አይንጋለት!

ጥበብን የተላበሱ ግን ደግሞ በጣም የተጋነኑ ምርቃቶች ደግሞ አሉ

- እስክሪብቶህ ይርዘም!
- ፊርማህ ማተብ ይሁን!
- ትንፋሽህ ይወፍር!

በአንዳንድ ቦታዎች ምርቃቶች ፈጽሞ ፈር እየሳቱ መጥተዋል። አንድ ወዳጄ እንደተናገረውና እኔም እንዳስተዋልኩት ያ የማይጠገበው የአባቶቻችንና የእናቶቻችንን ወግ ዛሬ የለም፤ አስተውሎቶቻቸውን በወግ መልክ ከማስተላለፍ ምርቃት ማዥጎድጎድ እየቀለላቸው መጥቷል። አንደበተ-ርቱዕነትና አስተዋይነትን ከሚጠይቀው ወግ አንፃር ከታየ ምርቃት የሰነፎች ሥራ ነው።

በስብሰባዎች በወያኔ የኦሮሚያና የደቡብ ክልሎች ምስለኔዎች - ኦህዴድና ደህዴድ - ተመርጠው የሚመጡ ‹‹ሽማግሌዎች›› ምርቃት እያሉ የሚያዥጎደጉዱት ወያኔን ማወደስና ተቃዋውሞን ማውገዝ ነው። ከሰማኋቸውን የስብሰባ ‹‹ምርቃቶች›› ጥቂት ላካፍላችሁ።

- ኢህአዴግ ምድሩና ሰማዩ እልል ብሎ ይቀበልህ!!
- ኢህዴግን በክፉ የሚያነሳ ብርሃን አይውጣለት!!!
- ኢህአዴግን የሚያማ ልጅ አይውጣለት!!!

እንደ እድር አይነት ባህላዊ ስብሰባዎች በምርቃት ቢከፈቱ አይደንቀኝም። የፓርቲ ስብሰባ በምርቃት መክፈት ግን ተሰብሳቢዎች መድረኩ ላይ ያሉት ሰዎች ለሚሉት ነገር ሁሉ ‹‹አሜን›› እንዲሉ ማመቻቸት በመሆኑ ፈጽሞ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም እላለሁ።

አንድ ተጨማሪ ምሳሌ ልስጥ። ‹‹መንግሥታችን ውሎ ይግባ!›› የማይቀር የስብሰባ ‹‹ምርቃት›› ነው። ይህችን ‹‹ምርቃት›› ለዘብተኛ የተባሉ ሽማግሌዎች እንኳን አይተዋትም። በዚህ ምርቃት ‹‹አሜን›› ብሎ የጀመረ ተቃዋሚ ከራሱ ጋር እየተጣላ አይደለምን?

ወያኔ በሥልጣን ላይ በቆየባቸው ጊዜዓት ሁሉንም ባህላዊ እሴቶቻችንን ለእሱ በሚስማማ መንገድ አበላሽቷቸዋል። የሽማግሌዎች ምርቃት ከእነዚህ እሴቶች አንዱ ነው። በተለይ በገጠር ወጣቶች በሥራ መትጋትን ትተው ምርቃት ሲፈፀም ለማየት በመጠባበቅ ባዶ ተስፈኛ እንዲሆኑ ተደርገዋል። በገጠር ለተሰማሩ ወያኔዎች ምርቃት ምናልባትም ዋነኛው የፕሮፓጋንዳ መሣሪያቸው ሳይሆን አይቀርም። ይህንን በከፍተኛ ጥንቃቄ መዋጋት የሥራችን አካል መሆን ይኖርበታል እላለሁ።